# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ

መመሪያ ቁጥር 167/2017

## የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት በመስጠት ለተሰማሩ አካላት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ እና የስራ ፈቃድ አፈጻጸም መመሪያ

መጋቢት 2017

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ የማጓጓዝ እና መልሶ የመጠቀምና ኡደት የማድረግ ስራዎችን በመንግስት አቅም ብቻ መስራት የማይችል መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የግሉ ዘርፍ እንዲሰማራ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ መሰረት በርካታ ደረቅ ቆሻሻ አገልግት ሰጪ አካላት ፈቃድ አውጥተው እንዲሰሩ በማስፈለጉ ፣

የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ እና መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ አገልግሎት ሰጪ አካላት የሚሰጡትን የአገልግሎት ጥራት ለመጨመር እና የሚፈጠሩ የአሰራር ግድፈቶችን በዘላቂነት ለማረም የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 100/2010 አንቀጽ 22(1) እና 33 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ሰጪ አካላት የብቃት ማረጋገጫ እና የስራ ፈቃድ አሰጣጥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 167/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ ወይም ሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) **"ኤጀንሲ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
   2) **"ደረቅ ቆሻሻ"** ማለት ከመኖሪያ ቤትና ከተቋማት የሚመነጭ ሆኖ በአመንጪው አካል ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማይፈለግ ተብሎ የሚጣል በይዘቱ ጠጣር ወይም ከፊል ጠጣር የሆነ ቁስ ነው፤
   3) **"መሰብሰብ"፡** ማለት ደረቅ ቆሻሻን ከመነጨበት ቦታ (ከቤት ለቤት) ሰብስቦ ወደ ጊዚያዊ ማቆያ ቅብብሎሽ ጣቢያ ማድረስ ማለት ነው ፡፡

4) **"ማጓጓዝ"፡** ማለት ደረቅ ቆሻሻን ከጊዜያዊ ማቀያ ቅብብሎሽ ጣቢያ ወይም ከተቋማት ወደ መጨረሻ መዳረሻ (ማስወገጃ ቦታ፣ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት ወይም ኃይል ማመንጫ ማዕከል) ማድረስ ማለት ነው ፡፡

5) **"የግል የጽዳት ድርጅት"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ከመኖሪያ ቤት ውጪ ከሆኑ የተለያዩ ተቋማት ደረቅ ቆሻሻን የመሰበስብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጥ በግል፣ በማህበር፣ በሽርክና፣ በዩኒዬን ወይም በተመሳሳይ መልክ የተደራጀ ድርጅት ነው፤

6) **አውትሶርስ ድርጅት** ማለት በአዲስ አበባ ከሚገኙ ጊዜያዊ ደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ጣቢያዎች ደረቅ ቆሻሻን ወደ መጨረሻ መዳረሻ ማዕከላት (ማስወገጃ ቦታ፣ ሀይል ማመንጫ ማዕከል ወይም መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ማዕከል) የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጥ በግል፣ በማህበር ወይም በተመሳሳይ መልክ የተደራጀ ድርጅት ነው ፡፡

7) **"የጽዳት ሽርክና ማኅበራት"** ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ከመኖሪያ ቤቶች ደረቅ ቆሻሻን ከቤት ለቤት በመሰብሰብ ጊዜያዊ ደረቅ ቆሻሻ ማቀያ ጣቢያ ድረስ የሚያደርሱ አከላት ናቸው ፤፤

8) **"የመልሶ መጠቀምና ኡደት ሽርክና ማኅበራት"** ማለት ደረቅ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀምና ኡደት በማድረግ ለተሰማሩ አካላት ተፈላጊውን የደረቅ ቆሻሻ ግብዓት (ወረቀት፣ ካርቶን፣ ፕላስቲክ፣ ወዘተ) የሚያቀርቡ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተደራጁ አካላት ናቸው ፡፡

9) **"ተሸከርካሪ"** ማለት ደረቅ ቆሻሻን በማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጥ ኮምፓክተር ተሸከርካሪ ነው ፤፤

10) **"የስራ ፈቃድ"** ማለት በጽዳት አስተዳዳር ኤጀንሲ ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ ወይም በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ላይ ለሚሰማሩ አካላት የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው፤፤

11) **"የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት በጽዳት አስተዳዳር ኤጀንሲ ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ ወይም መልሶ በመጠቀምና ኡደት ማድረግ ላይ ለሚሰማሩ አካላት በመስፈርቶች ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው ፤፤

12) **"ተቋም"** ማለት በከተማ ውስጥ ከመኖሪያ ቤት ውጭ የሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የገባያ ማዕከላት፣ ሆቴሎች፣ ሆስፒታሎች፣ አነስተኛና ከፍተኛ የንግድ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ወዘተ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

13) **"መልሶ መጠቀም"** ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ እቃዎችን በማውጣት በቀጥታ ወይም የተወሰነ ለውጥ አድርጎ እንደገና መጠቀም ወይም አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

14) **"ኡደት ማድረግ"** ማለት ደረቅ ቆሻሻን በጥሬ እቃነት በመጠቀም ከመጀመሪያው ጋር የሚመሳሰል ወይም የማይመሳሰል ጠቃሚ እቃ ማምረት ነው፡፡

15) **ጊዜያዊ ደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ጣቢያ** ማለት ከመኖሪያ ቤት የተሰበሰበ ደረቅ ቆሻሻን ለተወሰነ ሰዓት ለማከማቻነት ወይም ለማቆያነት የሚያገለግል በጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እውቅና ወይም ህጋዊ ፈቃድ የተሰጠው ቦታ ማለት ነው ፡፡

3. <u>**የጾታ አገላለጽ**</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

4. <u>**የመመሪያው ወሰን**</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ከመኖሪያ ቤቶችና ከተቋማት ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብና በማጓጓዝ እና መልሶ በመጠቀምና ኡደት በማድረግ አገልግሎት ላይ በተሰማሩ አካላት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት፣ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ እድሳትና ስረዛ</u>

5. **የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት**

1) ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ ወይም መልሶ በመጠቀምና ኡደት በማድረግ ላይ ለመሰማራት ጥያቄ ለሚያቀርቡ አካላት በመስፈርት መዝኖ የብቃት ማረጋገጫ እና የስራ ፈቃድ ይሰጣል፤ እድሳት ያደርጋል ፤

2) የስራ ፈቃድ መስጠትን ወይም እድሳት ማድረግን እንደ አስፈላጊነቱ ለክፍለ ከተማ ወይም ለወረዳ ሊያስተላልፍ ይችላል፤

3) ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የሚያግዙ የተለያዩ የአሰራር ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፤

4) ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ሰጪ አካላት ስራቸውን በአግባቡ እያከናወኑ መሆኑን ይከታተላል፤

5) ይህ መመሪያ በአግባቡ መፈጸሙን በመከታተል አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

6) የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎቱን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በማይሰጡ አካላትን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊዉን እርምጃ ይወስዳል፤

7) የስራ ፈቃድ ከወሰዱ አካላት ጋር ህጋዊ የስራ ውል ሰነድ ይፈራረማል፡፡

8) የከተማዋን ሁለንተናዊ ጽዳት ለማስጠበቅ የሚያስችለ ሥራዎችን ያከናውናል፤ ከሚመለከታቸው አካላት መዝኖ የብቃት ማረጋገጫ እና የስራ ፈቃድ ይሰጣል፤ እድሳት ያደርጋል ፤

## 6. የብቃት ማረጋገጫ ለማገኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

1) ከመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ (የጽዳት ሽርክና ማህበራት)የብቃት ማረጋገጫ ለማገኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፤

ሀ/ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው የምስክር ወረቀት ያላቸው ፤፤

ለ/ እያንዳንዱ ሽርክና ማህበር ከቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብ አገልግሎቱን በጥራት ለመስጠት ቢያንስ 8 ሜትር ኩብ እና ከዚያ በላይ የመጫን አቅም ያላቸው አይሱዙ ወይም ሌላ አራት ጎማ ተሽከርካሪ ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፡፡ አዲስ የተቋቋሙ ሽርክና ማህበራት ከሆኑ የፋይናንስ አቅማቸው እስኪያድግ ድረስ እስከ ስድስት ወር ከዚህ መስፈርት ነጻ ሆነው በኪራይ መስራት ይችላሉ

ሐ/ የማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ/ሰነድ ፤፤

መ/ አገልግሎቱን በስታንዳርድ ለመስጠት የሚያስችል ቢያንስ 25 አባለት ያሉት ማህበር መሆን አለበት ፡፡

ሠ/ የስራ ላይ ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት ማሟላት አለበት (ቱታ፣ አንጸባራቂ ልብስ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ፣ የእጅ ጓንት፣ሴፍቲ ጫማ እና ሂልሜት)፤

2) ደረቅ ቆሻሻ በማጓጓዝ (የአውትሶርስ /የግል ጽዳት ድርጅቶች) የብቃት ማረጋገጫ ለማገኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፤

ሀ/ በዚህ አገልግሎት በማኅበር የተደራጁ ወይም በግል መሳተፍ ይችላሉ ፤

ለ/ ደረቅ ቆሻሻ የማጓጓዝ አገልግሎት ለመስጠት የሚሰማራ ማንኛውም አካል ቢያንስ እያንዳንዳቸው 40 ሜትር ኪዩብ የመጫን አቅም ያላቸው ሁለት

ኮምፓክተር ተሽከርከሪዎች በራሱ፤በኪራይ ወይም አንዳንድ መኪና ያላቸው ለሁለት በጥምረት ሊኖራቸው ይገባል ፤

ሐ/ የሚያቀርባቸው ደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ኮምፓክተር ተሽከርካሪዎቹ የራሱ ከሆኑ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ በኪራይ ከሆኑ ከውልና ማስረጃ ሰነዶች ማረጋገጫ ኤጀንሲ የኪራይ ውል ማስረጃ ማቅረብ አለበት ፤

መ/ አዲስ ለሚገቡ ድርጅቶች የሚያቀርባቸው ኮምፓክተር ተሽከርካሪዎች የስሪት ዘመናቸው ከ20 ዓመት ያልበለጠው መሆን አለበት ፤

ሠ/ አዲስ ለሚገቡ ድርጅቶች ኮምፓክተር ተሽከርካሪዎቹ ተሰርተው ለአገልግሎት ከዋሉበት ጊዜ ጀምሮ በአመት ከ50,000 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ በአጠቃላይ በ20 አመታቸው ውስጥ ከ1,000,000 ኪሎ ሜትር በላይ ያልተጓዙ መሆን አለባቸው፡፡

ሠ/ የኮምፓክተሮቹ ቆሻሻን የማመቅ አቅማቸው በሬሽዮ ሲገለጽ 1ለ4 (1፡4) እና ከዚያ በላይ የሆነ ማለትም አራት ያህል የቆሻሻ መለኪያ መጠን ወደ አንድ የመጭመቅ አቅም ያላቸው እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት ፤

ረ/ ለአንድ ተሽከርካሪ ቢያንስ አንድ ሹፌርና አንድ ረዳት ማሟላት አለበት፤

ስ/ ለሰራተኞቹ የስራ ላይ ደህንነት መጠበቂያ አልበሳት ማሟላት አለበት (ቱታ፣ አንጸባራቂ ልብስ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ፣ የእጅ ጓንት፣ሴፍቲ ጫማ እና ሄልሜት) ፡፡

3) ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ የሚያስፈልጉ ደረቅ ቆሻሻ ግብዓቶችን በመሰብሰብና ማጓጓዝ የሚጠቀሙ ግለሰብ /የመልሶ መጠቀምና ኡደት ሽርክና ማህበራት/ የብቃት ማረጋገጫ ለማገኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፤

*ሀ) ለግለሰብ*

1) የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የንግድ ስራ ፍቃድ፣የግብር ከፋይ የምዝገባ ሰርተፊኬት ዋና እና ኮፒ ማቅረብ አለበት
2) ለስራው የሚያስፈልጉ የስራ መሳሪዎች(ሚዛን ፣ መቆራረጫ፣ ቅርፅ ማውጫ እና የመሳሰሉት) አንድ እና ከዚያ በላይ ያለው
3) የመልሶ መጠቀምና ኡደት የሚውል ግብዓት መሰብሰቢ /ማከማቻ/ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም የኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል) ማቅረብ የሚችል

*ለ) ለማህበር*

1) በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው የምስክር ወረቀት ያላቸው
2) የማህበሩ መመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ አለበት
3) ለማሰባሰቢያ የሚያገለግል ከ25 በላይ ፎዴ (ከ800 ኪ.ግ በላይ ሊይዝ የሚችል ማጠራቀሚያ ከረጢት) ያለው
4) ለኮምፖስት ማህበራት ለምርት ማከማቻ/መያዣ የሚሆን በማህበሩ ስም የታተመ 80ከረጢት/ማዳበሪ እያንዳንዳቸው 100ኪሎግራም የመያዝ አቅም ያለው
5) አገልግሎቱን መስጠት የሚያስችል የተሟላ የሰው ሀይል (የወረቀት ቢያንስ 5 ፣ ለኮምፖስት 10 እና ከዚያ በላይ ፣ ለፕላስቲክና ሌሎች 10 ከዚያ በላይ አባላት) ያሉት ማህበር ሊሆን ይገባል፣
6) የስራ ላይ ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት ማሟላት አለበት (ቱታ፣ አንፀ ባራቂልብስ፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ፣የእጅ ጓንት፣ሴፍቲ ጫማ እና ሄልሜት)

4) ደረቅ ቆሻሻ መልሶ በመጠቀምና ኡደት በማድረግ ላይ የብቃት ማረጋገጫ ለማገኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፤

ሀ) በኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተሰጠ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ዋና እና ኮፒ፤

ለ) ቆሻሻን መልሶ ኡደት ለማድረግ የሚጠቅሙ ማሽነሪዎች (መፍጫ ማሽን፣ መጨፍለቂያ ማሽንና የመሳሰሉት) ሁለት እና ከዚያ በላይ ያለው፤

ሐ) የመልሶ መጠቀምና ኡደት የሚውል ግብዓት እና የምርት ማከማቻ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም የኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል) ማቅረብ የሚችል፤

መ) ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ የሚውል የደረቅ ቆሻሻ ግብዓት መቀበያ ድጅታል የምድር ሚዛን ያለው፤

ሠ) ለሰራተኞቹ የስራ ላይ ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት ማሟላት አለበት (ቱታ፣ አንጸባራቂ ልብስ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ፣ የእጅ ጓንት፣ሴፍቲ ጫማ እና ሄልሜት)፤

ረ) በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የተሰጠ የብክለት ቁጥጥር ሰርትፍኬት ሊኖረዉ ይገባል፤

## 7. የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት አሰጣጥ ሂደት

ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ ወይም መልሶ በመጠቀምና ኡደት በማድረግ የብቃት ማረጋገጫ ማገኘት የሚፈልግ አካል፡-

1) ኤጀንሲው ያስቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ መክፍል ይኖርበታል፤
2) በኤጀንሲው በጥናት እና ፕሮጅክት አሰተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ በመገኘት ለዚሁ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ መሙላትና የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበትን ደረሰኝ በማያያዝ ለጥናት እና ፕሮጅክት አሰተዳደር ዳይሬክቶሬት ማቅረብ አለበት፤
3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.1፣ 6.2፣ 6.3 ወይም 6.4 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የቀረበው ማስረጃ ትክክለኛነት የግል ጽዳት ድርጅቶች የአሰራር መመሪያ ቁጥር 23/2013 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በኤጀንሲው የሚቋቋመው ቴክኒካል ኮሚቴ ከተረጋገጠ በኋላ ጥያቄው በቀረበ በ10 ቀናት ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፍኬቱ ይሰጣል፡፡

## 8. <u>የሥራ ፈቃድ ለማገኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች</u>

1) ከመኖሪያ ቤቶች ደረቅ ቆሻሻ ለመሰብሰብ የሚሰጥ የስራ ፈቃድ መስፈርቶች (ለጽዳት ሽርክና ማህበራት)

ሀ/ ከኤጀንሲው የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት፤
ለ/ የታደሰ የንግድ ፈቃድ /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤
ሐ/ የታደሰ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤
መ/ የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር (TIN) /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/።

2) ደረቅ ቆሻሻ ለማጓጓዝ (አውትሶርስ/የግል ጽዳት ድርጅቶች) የሚሰጥ የስራ ፈቃድ መስፈርቶች

ሀ/ ከኤጀንሲው የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት፤
ለ/ የታደሰ የንግድ ፈቃድ /ዋናው እና ፎቶ ኮፒ/፤
ሐ/ የታደሰ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤
መ/ የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር (TIN) /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤
ሠ/ አመታዊ የተሸከርካሪዎች የቴክኒካል ምርመራ ወረቀት /ዋናው እና ፎቶ ኮፒ/፤

ረ/ የባለቤቱ ወይም የስራ አስኪያጁ የታደሰ የነዋሪነት መታዋቂያ /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤

ሰ/ በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት የተደራጁ ከሆኑ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የምስክር ወረቀት ዋናውና ኮፒ፤

ሸ/ ለመስሪያ ቦታ የሚያገለግል የቤት ኪራይ ውል ወይም የግል ቤት ከሆነ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማቅረብ የሚችል፤

**3) ለመልሶ ለመጠቀምና ኡደት ማድረግ ግብዓት ለሚያሰባስቡና ለሚያቀርቡ (የመልሶ መጠቀምና ኡደት ሸርክና ማህበራት) የሚሰጥ የስራ ፈቃድ መስፈርቶች**

ሀ/ ከኤጀንሲው የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት፤

ለ/ የታደሰ የንግድ ፈቃድ /ዋናው እና ፎቶ ኮፒ/፤

ሐ/ የታደሰ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤

መ/ የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር (TIN) /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/።

ሠ/ በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት የተደራጁ ከሆኑ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የምስክር ወረቀት ዋናውና ኮፒ፤

**4) ደረቅ ቆሻሻ መልሶ በመጠቀምና ኡደት በማድረግ ለሚሰማሩ አካላት የሚሰጥ የስራ ፈቃድ መስፈርቶች**

ሀ/ ከኤጀንሲው የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት፤

ለ/ የታደሰ የንግድ ፈቃድ /ዋናው እና ፎቶ ኮፒ/፤

ሐ/ የታደሰ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤

መ/ የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር (TIN) /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤

ሠ/ አመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒካል ምርመራ ወረቀት /ዋናው እና ፎቶ ኮፒ/፤

ረ/ የባለቤቱ ወይም የስራ አስኪያጁ የታደሰ የነዋሪነት መታዋቂያ /ዋናውና ፎቶ ኮፒ/፤

ሰ/ በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት የተደራጁ ከሆኑ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የምስክር ወረቀት ዋናውና ኮፒ፤

**9. የስራ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት**

ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ ወይም መልሶ በመጠቀምና ኡደት በማድረግ አገልግሎት ለመስጠት የስራ ፈቃድ የሚፈልግ አካል፡-

1. በኤጀንሲው ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት ቢሮ በመገኘት ለዚሁ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ መሙላት ይኖርበታል ፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 3 ወይም 4 የተጠየቁ መስፈርቶች ስለመሟላታቸው ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤
3. መረጃዎቹ ከተሟሉ የስራ ፈቃድ ጥያቄው በቀረበ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ይሰጣል ፤

## 10.የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ እድሳት ሁኔታ፤

1. የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ እድሳት በየአመቱ ይደረጋል፤
2. የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ እድሳት ማገኘት የሚፈልግ አካል በኤጀንሲው ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት ቢሮ በመገኘት ለዚሁ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ መሙላት አለበት፤
3. ኤጀንሲው ያስቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ መክፍል ይኖርበታል፤
4. የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበትን ደረሰኝ በማያያዝ ለዳይሬክቶሬቱ ማቅረብ አለበት፤
5. የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ እድሳት በየአመቱ ከሀምሌ 1 እስከ 30 ባሉት ቀናቶች ውስጥ ይከናወናል፤
6. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ወይም የስራ ፈቃድ እድሳት እንዲደረግለት የሚፈልግ አካል፡-

   ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና 9 የተቀመጡ መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤፤

   ለ/ ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ ወይም በማጓጓዝ የተሰማሩ አካላት የመልካም ስራ አፈጻጸም ደብዳቤ ከኤጀንሲው ዳይሬክቶሬቱ ማቅረብ ይኖርበታል፤
7. አስፈላጊ ማስረጃዎች ከተሟሉ የብቃት ማረጋገጫ ወይም የስራ ፈቃድ እድሳት ጥያቄው በቀረበ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ይሰጣል።

## 11.የተከለከሉ ተግባራትና ተጠያቂነት

1. ማንኛውም በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ለመስጠት የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ያገኘ አካል፡-

   ሀ/ ለአንድ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ዘርፍ ያገኘውን የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ሌላ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ዘርፍ መጠቀም አይችልም። ለምሳሌ ከቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብ አገልግሎት ለመስጠት ያገኘውን የብቃት

ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ደረቅ ቆሻሻ ለማጓጓዝ አገልግሎት ወይም ለደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ አገልግሎት መጠቀም አይችልም ፡፡

ለ/ አገልግሎት እየሰጠበት ያለውን የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ዘርፍ መቀየር የፈለገ እንደሆነ ወይም ሌላ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ዘርፍ በተጨማሪ መስራት ከፈለገ በዚህ መመመሪያ አንቀጽ 6 እና 8 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት ካልሆነ በስተቀር በሌላ መንገድ የአገልግሎት ዘርፍ መቀየር ወይም ተጨማሪ የአገልግሎት ላይ የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ማገኘት አይችልም፡፡

2. ማንኛውም አካል (ግለሰብም ይሁን ማህበር/ድርጅት) ከኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ሳያገኝ ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ ወይም መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ አይችልም ፡፡
3. ከኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ሳያገኝ ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብ፣ ሲያጓጉዝ ወይም መልሰ ሲጠቀምና ኡደት ሲያደርግ የተገኘ አካል በደንብ ቁጥር 167/2016 መሰረት ተጠያቂ ይሆናል ፡፡
4. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ካልፈፀመ አግባቢነት ባለዉ ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 12.የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ እገዳና ስረዛ

በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም ሥራ ፍቃድ እገዳ ወይም ስረዛ የሚፈጸመዉ በሚከተሉ ሁኔታ ነዉ፡-

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ወይም (ለ) ላይ የተቀመጠዉን አማራጭ ባለመጠቀም ወይም የተጣለውን ክልከላ በመተላለፍ በአንድ አገልግሎት ዘርፍ የተሰጠን የብቃት ማረጋገጫ ሌላ አገልግሎት ዘርፍ ሲጠቀም ከተገኘ በመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ማስተካካያ እርምጃ ካልወሰደ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ለ 1 ወር ይታገዳል ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ-1 መሰረት በተቀመጠው የእግድ ጊዜ ገደብ አስፈላጊውን ማስተካካያ ወስዶ ወደ ስራ እንዲመለስ በኤጀንሲው የብቃት

ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ለሚሰጠው አካል ፈቃድ ጠይቆ ወደ ስራ ካልገባ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

3. የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ሰጪዉ አካል ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወጪ በራሱ ፈቃድ ስራውን ካቋረጠ አጀንሲው የሰጠውን የብቃት ማረጋገጨና የስራ ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13.የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት፡-

1. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ እና መልሶ መጠቀምና ኡደት በማድረግ ለመሰማራት የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ የሚጠይቅ አካል በአሰራሩ ቅሬታ  ከላው ቅሬታውን ለኤጀንሲው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፤
2. የኤጀንሲው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ መፍትሄ እንዲሰጥበት ቅሬታው ለሚመለከተው አካል/ድፓርትመንት ይመራል፤ ቅሬታው ምላሽ እንዲያገኝ ይከታተላል፤ ለቅሬታ አቅራቢው አካል ቅሬታው በቀረብ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ምላሽ ይሰጣል፤
3. በኤጀንሲዉ መጨረሻ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ አካል አቤቱታዉን ስልጣን ወዳለዉ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ፡፡

### 14.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ የከተማው አስተዳደር መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት  ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 15.መመሪውያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ሲታመንበት ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 16.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በኤጀንሲው ድረ ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ መጋቢት 2017

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ጽዳት አስተዳደር አጀንሲ ኃላፊ